## የምድብ ዓይነቶች እና የቅይይር ስሌቶች ፡ ሁለት

## የቃላት ጥያቄዎች

1. 1ኪ.ሜ$^2$ ከየትኛው ምድብ ጋር እኩል ነው ?

   ሀ) 1000 ሜ$^2$ ለ) 100000 ሳ.ሜ$^2$

   ሐ) 1000000 ሚ.ሜ$^2$ መ) ሀ እና ለ

2. የሳሚ አባት ቁመት 2ሜ ነው፡፡ ሳሚ ደግሞ ቁመቱ 1ሜትር ከ 35 ሳ.ሜ ነው ፡፡ 20 ሳ.ሜ በርጩማ ላይ ቢወጣ የአባቱ ቁመት ላይ መድረስ ይችላል ወይስ አይችልም?

   ይችላል አይችልም

   2.1. የሳሚ ቁመት ከአባቱ ቁመት ምን ያህል ሳ.ሜ ልዩነት አለው ?

   ሀ) 15 ሳ.ሜ ለ) 5 ሳ.ሜ ሐ) 10 ሳ.ሜ መ) 0 ሳ.ሜ

3. በከፍተኛ ዝላይ ውድድር ላይ እያንዳንዱ አትሌት 3 ሜ የሚሆን ርቀት መዝለል አለበት ፡፡ ሶፊያ በመጀመሪያ ዝላይ 3.19 ሜ ዘለለች ፡፡ ሃና ደግሞ ሶፊያ ከዘለለችው ርቀት 35 ሳ.ሜ ጭማሪ ዘላለች፡፡ ሃና የዘለለችው ርቀት ስንት ሳ.ሜ ይሆናል ?

   ሀ) 35.4 ሳ.ሜ ለ) 3.54 ሳ.ሜ


   ሐ) 354 ሳ.ሜ መ) 0.354 ሳ.ሜ



4. ናሆም ቁመት 125 ሳ.ሜ ሲሆን የጓደኛው የሄኖክ ደግሞ 138 ሳ.ሜ ነው ፡፡ ከ 1 ዓመት በኋላ ናሆም 40 ሳ.ሜ ቁመት ሲጨምር ሄኖክ ደግሞ 25 ሳ.ሜ ቁመት ጨምሯል ፡፡ በናሆም እና በሄኖክ መካከል ምን ያህል ልዩነት አለ ?

   ሀ) 20 ሳ.ሜ ለ) 2 ሳ.ሜ ሐ) 0.02 ሜ መ) ለ እና ሐ

LIVEWORKSHEETS




5. ቀነኒሳ በ 20 ደቂቃ ውስጥ 1.2 ኪ.ሜ መሮጥ ከቻለ፣ በአንድ ደቂቃ ስንት ሜትር መሮጥ ይችላል ?

ሀ) 60 ሜ　　　ለ) 600 ሜ

ሐ) 120 ሜ　　　መ) 6 ሜ

6. አንድ የሸክላ ጡብ 12 ሚ.ሜ ውፍረት አለው ፡፡ 110 የሸክላ ጡቦች ተነባብረው ቢቀመጡ ምን ያህል ሜትር ቁመት ይሆናል?




ሀ) 60 ሜ　　　ለ) 600 ሜ

ሐ) 120 ሜ　　　መ) 6 ሜ

7. አንድ ኤሊ በ 27 ደቂቃ ውስጥ 567 ሚ.ሜ ትጓዛለች፡፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ምን ያህል ሳ.ሜ መጓዝ ትችላለች?



ሀ) 11 ሳ.ሜ　　　ለ) .21 ሳ.ሜ

ሐ) 2.1 ሳ.ሜ　　　መ) 21 ሳ.ሜ

8. የአንድ ላጲስ ውፍረት 10 ሚ.ሜ ቢሆን ፣ አንድ ባለሱቅ 230 ላጲሶችን ወደላይ ደርድሮ ለማስቀመጥ ምን ያህል ሴንቲ ሜትር ቁመት ቦታ ይወስድበታል ?




ሀ) 0.1 ሳ.ሜ　　　ለ) 23 ሳ.ሜ

ሐ) 2.3 ሳ.ሜ　　　መ) 0.23 ሳ.ሜ

9. አንድ የስጦታ እቃን ለማሸግ 20 ሳ.ሜ ሪቫን ይፈልጋል ፡፡ 6 ሜትር ሪቫን ምን ያህል የስጦታ እቃዎችን ማሸግ ይቻላል ?



ሀ) 45 ሳ.ሜ　　　ለ) 35 ሳ.ሜ

ሐ) 30 ሳ.ሜ　　　መ) 0.3 ሳ.ሜ

LIVEWORKSHEETS

10. 1.2 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 6 ሜትር ወርድ ያለውን የሰፈራችንን መንገድ ርዝመቱ 24 ሳ.ሜ እና ወርዱ 15 ሳ.ሜ በሆነ ሸክላ ለማንጠፍ ስንት ሸክላዎች ያስፈልጉናል ?



ሀ) 20,000 ለ) 2,000

ሐ) 120,000 መ) 200,000

11. የአንድ የመመገቢያ ክፍልን ለማንጠፍ ርዝመቱ 12 ሳ.ሜ ወርዱ ደግሞ 10 ሳ.ሜ የሆነ 100 ሸክላዎች ቢያስፈልገን የክፍሉ ስፋት ምን ያህል ሜ$^2$ ነው ?



ሀ) 1200 ሜ$^2$ ለ) 120 ሜ$^2$

ሐ) 12000 ሜ$^2$ መ) 12 ሜ$^2$

LIVEWORKSHEETS